# ሰማያዊው መጽሐፍ
# (The Blue Book)

Wisdom at the source of the Blue Nile

## የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ
## ራዕይ ጥበብ 2017 መንገድ

**ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ**
**ጥቅምት 2007 ዓ.ም**

## ማውጫ


መግቢያ ..... 1

1. የዩኒቨርሲቲዎች አፈጣጠር ..... 4

1.1. የመጀመሪያዎቹ የዓለማችን ዩኒቨርሲቲዎች አመሠራረት ..... 4

1.2. ለ.ዩኒቨርሲቲዎች በአውሮፖ የሕዳሴ ዘመን ..... 6

1.3. ዩኒቨርሲቲዎች በ21ኛው ክፍለ ዘመን ..... 6

2. የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አፈጣጠርና ባህሪያት ..... 9

3. የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጉዞ አቅጣጫ ..... 11

3.1. ምርጥ ተመራማሪና ምርጥ አስተማሪ የሞሉበት ተቋም መሆን ..... 11

3.2. ደረጃውን የጠበቀ ምርምርና ትምህርት መስጠት የሚያስችል መሰረተ ልማትና ግብአት መኖር፣ ..... 12

3.2.1. የምርምር በጀት ..... 12

3.2.2. የምርምርና ጥራት ያለው ትምህርት መስጫ ሌሎች ግብዓቶች መሟላት ..... 13

3.2.3. ጥራት ያላቸውና ለመማርና ለመመራመር የሚተጉ ተማሪዎች ይኖራሉ ..... 14

3.2.4. የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመመስረት የቀረጠና ግልጽ ራዕይና ስትራቴጂ ያለው አመራር መኖር ..... 14

4. የጉዞ አቅጣጫችን የተመረጠበት ምክንያቶች ..... 16

5. ወደመረጥነው አቅጣጫ የሚወስዱን ስልቶች ..... 18

5.1. ምርጥ ምሁራን በበቂ ሁኔታ የምንፈጥርበት አግባብ ..... 18

5.2. ምርጥ ተማሪዎችን የምናገኝበት አግባብ ..... 20

5.3. መሠረተ ልማት ማሟላት ..... 22

5.4. ራእይ ያለውና ተግባርን መለኪያ ያደረገ አመራር መፍጠር ..... 24

6. ስልቶቻችን በተግባር የምንፈትሽባቸው አግባቦች ..... 26

7. የትውልድ ቅብብሎሽ የሚስተናገዱባቸው አግባቦች ..... 27

8. የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ..... 29

ማጠቃለያ ..... 30

# መግቢያ

በሦስተኛው ሚሊኒየም ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ወደነበረችበት ገናና ስሟ ለመመለስና የዓለም አቀፉ የግንኙነት ስበት ማዕከል እንድትሆን ለማድረግ በሁለተኛው ሚሊኒየም ማጠናቀቂያ ላይ የተገኘው ትውልድ ቃል ገብቷል፡፡ እናም ሀገራችን ኢትዮጵያ ከነበረችበት የድህነትና ኃላቀርነት ቀለበት ወጥታ በ2017 ዓ.ም. መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት አንዷ ለመሆንና ብሎም በምስራቅ ኤሲያ እንደታየው ሁሉ አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ ከበለጸጉት ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ ራዕይ ሰንቃ መንቀሳቀስ ከጀመረች የተወሰኑ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በነዚህ ዓመታት ውስጥ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በመሰረተ ልማትና በመሳሰሉት ዘርፎች በኢትዮጵያ ሁኔታ ሊፈጸሙ ቀርቶ ሊታሰቡ የሚከብዱ የሚመስሉ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችላለች፡፡ ይህ የልማት ዕንቅስቃሴ በውስን ዘርፎችና ተዋናዮች ብቻ የታጠረ ሳይሆን ምላዓተ ህዝቡን ያንቀሳቀሰ በመሆኑ በለውጥ ሂደቱ ውስጥ አስተዋጽኦ የማያበረክት ዜጋ እንደሌለ ማስተዋል ይቻላል፡፡

በተለያዩ ዘርፎች እየተደረጉ ያሉት እነዚህ እንቅስቃሴዎችና የተመዘገቡ ዕመርታዎች በትምህርት ዘርፉም በግልጽ የሚታዩ ናቸው፡፡ በሀገሪቱ እስከቅርብ ገዜ ድረስ አንድና ሁለት የነበሩት ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር በአጭር ግዜ ውስጥ ከሠላሳ በላይ መድረሱና ጥቂት ሺዎች የነበረው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ቅበላም ወደመቶሺዎች ማድግ መቻሉ የዚህ ፈጣን ለውጥ ውጤት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሊማሩ የሚችሉ ወጣቶች ቁጥር በፍጥነት እያደገ ሲሆን ይህም በቀጣይ የበለጠ በእንደሚገዝፍ የሚጠበቅ ነው፡፡ በሀገሪቱ ሊመጣ የሚጠበቀው ለውጥ የተማረ የሰው ኃይልን በብዛት በማፍራት ብቻ ሳይሆን በጥራትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ባረጋገጠ አግባብ መሆን ስላለበት ዩኒቨርሲቲዎች ሠፊ ሥራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገርም አገሪቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ 100 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ካላቸው ጥቂት ሃገራት የምትካተትና ከዚህም ውስጥ አብዛኛው ወጣትና በትምህርት ማለፍ የሚጠበቅበት ከመሆኑ አኳያ የዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር የበለጠ መበራከት የሚጠበቅባት አገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ስትሰለፍ የሚኖረው የዩኒቨርሲቲዎች ገጽታም በተመሳሳይ መልኩ የሚለወጥ በመሆኑ አገሪቱ ከዩኒቨርሲቲ ትምህርት አኳያ የምትደርስባቸውን ዒላማዎች አሁን በመካከለኛ ገቢ ደረጃ ካሉ አገሮች ደረጃ በመውሰድ

ማመላከት ይቻላል። ለምሳሌ የደቡብ አፍሪካ አካባቢ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበር ባወጣው መረጃ መሰረት ቦትስዋና እ.ኤ.አ በ2005/6 ከአጠቃላይ ምርቷ (GDP) 3.3% ያህል ለትምህርት ዘርፍ የምታውል ሲሆን ከዚህ ውስጥ ደግሞ 12.5% ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲመደብ ታደርጋለች። ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞም በዚሁ አመት የነበረው የምርምር በጀት ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት አኳያ የነበረው ጥመርታ 0.43% እንደነበር እንዲሁም የISI Web of Science ተጠቃሽ የሆኑ 280 ህትመቶች ከ1990 — 1995፣ 648 ያህል ከ1996 — 2001 እና 2002 — 2007 ባለው ጊዜ ደግሞ 948 የምርምር ውጤቶች ህትመትን ያሳኩ ዩኒቨርሲቲዎች ባለቤት ናት።

መካከለኛ ገቢ ያላቸው የሚባሉት አገሮች በዝቅተኛው ዕርከን እነግብጽ፣ ደ/አፍሪካ፣ ጋና፣ ህንድ የመሳሰሉትን እንዲሁም በከፍተኛው ዕርከን እነኩባ፣ አንጎላ፣ ብራዚል፣ ቱርክ፣ ማሌዢያ የመሳሰሉት የሚያቅፍ ሲሆን የከፍተኛ ትምህርት ደረጃችን በተለይ በአንፃራዊነት ቀዳሚ የሚባሉ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ከነዚህ አገራት ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር የሚወዳደሩ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ከነዚህ ቀድመው ተወዳዳሪነታቸውን ማረጋገጥ ከሚገባቸው የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ደግሞ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አንዱ ሲሆን እንደሚገባ ምንም ጥርጥር የለውም።

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 በአፍሪካ ካሉት ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን እንደግብጽና ደ/አፍሪካ ያሉ የተሻሉ ዩኒቨርሲቲዎችን ሁኔታ መፈተሽ ይኖርበታል። ይህም ሲሆን ነው በቀሪው ጊዜ ምን ያህል መራመድ እንደሚገባው መረዳት የሚቻለው። ዩኒቨርሲቲው አሁን በአለም አቀፍ ደረጃ ዕይታ ውስጥ ካሉት የነዚህ አገር ዩኒቨርሲዎች አኳያ ሲታይ እጅግ ወደኋላ የሚገኝ በመሆኑ ያለመታከት ለተከታታይ ዓመታት ብዙ መስራትን የሚጠይቅ ነው። ይህ ደግሞ መዳረሻን ለይቶ በማስቀመጥ የሚመራ እስከሆነ ድረስ የማይሳካበት ምንም ሁኔታ የለም። በ2013/14 በUniversity Ranking by Academic Performance (URAP) የተባለው መዛኝ *(ጥቅም ላይ የዋሉ መመዘኛዎች - Number of Articles, Citation, Total Document, Journal Impact Total, Journal Citation Impact Total, International Collaboration)* ባወጣው ደረጃ በግብጽ ካይሮ ዩኒቨርሲቲ 434ኛ፣ ኤን ዩኒቨርሲቲ 629ኛ፣ ማንሱራ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ 867ኛ ላይ የተቀመጡ ሲሆን፣ በጋና የጋና ዩኒቨርሲቲ 1250ኛ፣ በደ/አፍሪካ ደግሞ የኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ 231ኛ፣ ዊትወተርሰራንድ 339ኛ፣ ስቴልነቦሽ 411ኛ እንዲሁም ኩዋዙሉናታል 444ኛ ደረጃ ላይ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች መሆናቸው መስክሮላቸዋል። በዚህ

ንጽጽር ከሀገራችን የተሻለ ሆኖ የተገኘው ዩኒቨርሲቲ 1220ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው አንጋፋው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መሆኑ ሲታይ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲን ራዕይ ለማሳካት ፈጣን ግስጋሴ የሚጠይቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ በመካከለኛ ገቢ ውስጥ ያሉ አገሮች በረጅም ሂደት የገነቡትን አቅም በተነፃፃሪ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመገንባት ውጤቱን ማምጣት የሚቻል በመሆኑ ላይ ሁሉም ተዋናይ ማመንና ለዚሁም መንቀሳቀስ ይገባዋል፡፡ ይህ የዩኒቨርሲቲው የወደፊት አቅጣጫ በሰማያዊ መጽሐፍ መልክ ሲነደፍም ታሳቢው ሁሉም የዩኒቨርሲቲው አካል ቀጣይ የጉዞ መስመሩን ተረድቶና ተመሳሳይ ግንዛቤ ፈጥሮ ለውጤት እንዲባረብ በማሰብ ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጠቅለል ያለ የዩኒቨርሲቲዎች አፈጣጠርና በተለይም ደግሞ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ዕድገትና ባህሪያት፣ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቀጣይ የጉዞ አቅጣጫና የተመረጠበት ምክንያትና ውጥኑን ለማሳካት የተመረጡ ስልቶች በአጭር በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

# 1. የዩኒቨርሲቲዎች አፈጣጠር

## 1.1. የመጀመሪያዎቹ የዓለማችን ዩኒቨርሲቲዎች አመሠራረት

አለማችን የመጀመሪያ የሆነውን ዩኒቨርሲቲ የትና መቼ መሠረተች የሚለው ጭብጥና በሂደትም በአሁኑ ወቅት ያሏትን በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች እንዴት አገኘች የሚለው ጉዳይ ላይ የተለያዩ እይታዎች አሉ፡፡ አለማችን የመጀመሪያ የሆኗትን ዩኒቨርሲቲዎች ያየችው በአረቡ አለም ውስጥ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በሞሮኮ ሀገር የሚገኘው ካሩኢን ዩኒቨርሲቲ (University of Karueein) እ.አ.አ 859 በመመስረት የአለማችን የመጀመሪያ ዩኒቨርሲቲ እየተባለ ይነገርለታል፡፡ ይህ ተቋም መሠረቱ የማድራስ (Madrasa) ትምህርት ቤት እንደሆነና ዋናው ትኩረትም የእስላማዊ ሀይማኖትና ህግን በማስተማርና የአረብኛ ቋንቋ ህግጋትን በማስጨበጥ ላይ ያተኮረ ትምህርት ይሰጥ እንደነበረ ይገለፃል፡፡ በግብጽ ሀገር የሚገኘው አልአዛር ዩኒቨርሲቲ (Al-Azhar University) እ.አ.አ በ972 በመቋቋም አለማችን በሁለተኛ ደረጃ ያየችው ተቋም እየተባለ የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህ ተቋም የአረብኛ ቋንቋንና የእስልምና ሀይማኖትን ከማስተማር በተጨማሪ የሳይንስ ትምህርትም ያስተምር እንደነበረ ይነገራል፡፡

አለማችን በምዕራቡ አለም ያየችው የመጀመሪያ ዩኒቨርሲቲ በጣሊያን ሀገር እ.አ.አ 1088 የተመሠረተውን የቦሎኛ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ ይህ ዩኒቨርሲቲ የሮማውያንን የህግ ስርዓት ማስተማርን ጨምሮ ቋንቋም ያስተምር እንደነበር ይጠቀሳል፡፡ የዚህ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ይከፈላቸው የነበረው ክፍያ ከተማሪዎቻቸው የሚገኝ ስጦታ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዛን ጊዜ የፈጣሪ ስጦታ ተደርጐ የሚወሰደውን ሳይንስ መሸጥ አይቻልም ነበርና ነው፡፡

እዚህ ላይ በቦሎኛ ዩኒቨርሲቲ በ12ኛ ክፍለ ዘመን አንድ መሠረታዊ ጥያቄ መነሳቱን መጥቀስ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ እሱም በመንግስትና በቤተ-ክርስቲያን መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነትና መንግስቱ ሊከተለው ስለሚገባ ህግና የዩኒቨርሲቲው ነፃነት የተመለከተ ነበር፡፡ በዛን ጊዜ የነበሩት መሪ ከምሁራኑ ያገኙት ምክር ብቸኛው ህግ የሮማን ህግ መሆን እንደሚገባ ነበር፡፡ መሪውም ምሁራኖች ከሐይማኖትም ሆነ ከፖለቲካ ነፃ በሆነ አግባብ ማስተማራቸውንና መመራመራቸውን እንዲቀጥሉና መንግስትም ጥበቃ እንደሚያደርግ የወቅቱ መሪ ፍሬዲሪክ ባርባሮሳ ወሰኑ፡፡ ይህ ውሳኔና አቅጣጫ በአሁኑ ወቅት ላሉ ዩኒቨርሲቲዎች የአካዳሚክ ነፃነት መሠረት ሆነ፡፡ በተለይ የአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች ይህን መሠረታዊ ግንዛቤ በሚገባ ተጠቅመውበታል፡፡ በመሆኑም መንግሥት የዩኒቨርሲቲዎችን የአካዳሚክ ነፃነት እንዲያከብርና

እንዲያስከብር የሚለው ሐሳብ ገዥ ሆኖ ወጣ። እዚህ ላይ የአካዳሚክ ነፃነት የሚባለው ፅንሰሃሳብ ግልፅ መደረግ ያለበት ነው። የአካዳሚክ ነፃነት የሚባለው ፅንሰሃሳብ በሁለት ወገኖች ማለትም በአንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናትና አካዳሚሽያንስ ፅንፍ የያዙ ትርጓሜዎች ሲሰጡት ይስተዋላል። በመንግስት ባለስልጣናት በኩል የአካዳሚክ ማህበረሰብ በማንኛውም መልኩ መንግስትን ከመደገፍ ያለፈ ትችት ወይም ነቀፋ እንዲያሰማ የማይፈልጉ ሲሆን አካዳሚሽያኖች ደግሞ የአካዳሚክ ነፃነት ማለት መንግስትን ያለአካዳሚዊ አግባብ በዜግነታቸው ያላቸውን መብት በማንኛውም ጊዜ በተማሪዎቻቸው ላይ ማንፀባረቅና መጫን አድርገው ይተረጉሙታል።

ይሁን እንጅ የአካዳሚክ ነፃነት ማለት አካዳሚሽያን በዜግነቱ ከሚያገኘው የመደገፍና የመቃወም መብት እራሱን ከፍ አድርጎና አልቆ ከሚያስተምረው/ ሙያዊ የትምህርትና እውቀት አግባብ ተነስቶ ወይም በምርምር ከደረሰበት ተጨባጭ ዕውነታ ተነስቶ የመንግስትን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ አደረጃጀትና አሰራር በሳይንሳዊ ትንተና ተመስረቶ ልዩ ልዩ አማራጮችን በመዘርዘር የማሻሻያ፤ የማስተካከያ፣ የማጠናከሪያ ሂስ ማቅረብ መቻልን ያመለክታል። ይህም ሲሆን ተማሪዎች ከቀረቡላቸው አማራጮችና ትንተናዎች ተነስተው እውቀት እንዲጨብጡ፥ በራሳቸው ሚዛንም ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የማስቻል ነፃነትን የሚያመለክት ነው።

በእንግሊዘኛ ተናጋሪው የምዕራቡ አለም የመጀመሪያ ዩኒቨርሲቲ ተደርጐ የሚወሰደው እ.አ.አ 1096 ዓ.ም የተመሠረተውና በእንግሊዝ ሀገር የሚገኘው የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ነው። ይህ ተቋም በአሁኑ ወቅትም ጠንካራ ቁመና ያለውና ከአለም ግንባር ቀደም ተቋም አንዱ ለመሆን የበቃ ነው።

እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት በሀይማኖት ተቋሞች ስር የነበሩና አሁንም ያሉ ትምህርት ቤቶች በአገራችን የመጀመሪያ ዩኒቨርሲቲዎች ሊባሉ የሚችሉ መሆናቸው ነው። እነዚህ የመጀመሪያ የትምህርት ተቋሞች ተማሪዎቻቸው እንዲያነቡ፣ በሃይማኖታቸው ዙሪያ ሚስጥራትን እንዲገነዘቡና እርስ በርስ በመማማርና መጽሐፍትን በጥልቀት እንዲመረምሩ በማድረግ ዓለማዊና ኃይማኖታዊ ግንዛቤያቸው እንዲሰፋ ሲያደርጉ ቆይተዋል። በወቅቱም ተቋማቱ የመንግስት ሠራተኛ፣ የቤተ-እምነቶች መምህራንና አገልጋዮች፣ ዳኛና መሪዎችን በማፍራት ለማህበረሰብ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

## 1.2. ለ.ዩኒቨርሲቲዎች በአውሮፖ የሕዳሴ ዘመን

የአውሮፖ የሕዳሴ ዘመን ከ14ተኛው ክፍለ ዘመን እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን እንደተካሄደ ይነገራል፡፡ ይህ ታላቅ የባህል እንቅስቃሴ ሥነ-ጥበብ፣ ሳይንስና ፖለቲካ የሚሠራበትን አግባብና የማኅበረሰቡን አጠቃላይ ባህል በመሠረታዊነት የቀየረ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ዘመኑ የላቲን ሥነ-ጽሑፍ ያበበትና የትምህርት አሰጣጥም በመሠረታዊነት የተቀየረበት ዘመን ነበር፡፡ ዲፕሎማሲና ዴሞክራሲ መሠረት ያደረገ ፖለቲካና ተጨባጭ ሁኔታዎች ምልከታ ላይ የተመሠረተ ሳይንስም መሠራት የጀመረው በዚህ ዘመን ነው፡፡ የሰው ልጅ ዕድገት፣ ብልጽግናና ነፃነትም ተቀባይነትና ትኩረት ያገኘበት ዘመን ነበር፡፡

በዚህ ዘመን ዩኒቨርሲቲዎችም የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ቁሳዊ፣ ሃሳባዊ፣ ሞራላዊና መንፈሳዊ ብልጽግና ያለው ሕይወት እንዲመሩ የማብቃትና በአጠቃላይ የማኅበረሰብ ዕድገት እንዲመጣ መስራት የተጀመረበት ነው፡፡ ሥርዓተ ትምህርቶችንም ግልጽ ለሆነ ሙያ በሚያበቃ ሁኔታ መቀረጽ ተጠናከሮ የወጣበት ጊዜ ነበር፡፡፡ ሰብአዊ መብትና ዓለማቀፍ ሕግጋትም በወቅቱ ከአውሮፖ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ትኩረት ያገኙ መስኮች ሆነው ነበር፡፡ በተለይ እ.ኤ.አ 1492 አውሮፖዊያን አሜሪካ መኖሯን ማወቃቸው በርካታ ለዩኒቨርሲቲ መወያያና መማሪያ የሚሆኑ ሐሳቦችን እንዲፈጠሩ አስችለዋቸዋል፡፡ 16ተኛው ክፍለ ዘመን በርካታ ኅትመቶች መሰራጨትና የመረጃ ልውውጡ የተበራከተበት ዘመን ነበር፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በ18ኛው ክፍለ ዘመን ለተፈጠረው ዩኒቨርሲቲዎች መነቃቃት መሠረት ሆኗል፡፡ በተለይ በጀርመን ሀገር በነበሩ ዩኒቨርሲቲዎች የተፈጠረው ዩኒቨርሲቲዎችን ዕውቀት ከመጠበቅና ከማስተላለፍ ባለፈ ዕውቀትን የመፍጠርና የማበልፀግ ሥራ የመስራት ግንዛቤ ዓለማችንን በመሠረታዊነት ለቀየሩና እየቀየሩ ላሉ ሐሳቦችና ቴክኖሎጂዎች መሠረት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች መሃይምነትን የማጥፋት ቁንፅል አላማ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ያደገና የሰፋ ተልዕኮ ያላቸው መሆኑ የተሰመረበት ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

## 1.3. ዩኒቨርሲቲዎች በ21ኛው ክፍለ ዘመን

የዩኒቨርሲቲዎች ገጽታና ሚናቸው ባለንበት ዘመን በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ሁሉም በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ተልዕኳቸውን በምናይበት ወቅት በአብዛኛው ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህም ተልዕኮዎች ዕውቀት መጠበቅ፣ ዕውቀት ማስተላለፍ፣ ዕውቀት ማዳበርና የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ተመሳሳይነት ያለው ተልዕኮ ቢኖራቸውም እንደሚገኙበት አካባቢና የመንግስት ባህሪ በአፈፃፀምና በአሰራር ይለያያሉ፡፡

እዚህ ላይ ዕውቀትና ዕውቀት መጠበቅ እንዲሁም የማህበረሰብ አገልገሎት የሚባሉትን ነጥቦች በሰፋትና በጥልቀት መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ዕውቀት ስለአካባቢያችንና ስለዓለማችን በቂ ግንዛቤ ከማስጨበጥ በዘለለ የሰውልጅ መሰረታዊ አኗኗር የሚቀይር ችግር መፈቻና የብልፅግና ቁልፍ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዩነቨርሲቲ ደረጃ የምንይዘው፣ የምንጠብቀውና የምናስተላልፈው እውቀት የጠለቀና የሰፋ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ውሻ ስጋ በል እንደሆነ ፈረስ ደግሞ የማያመሰኳ ሳር በል እንሰሳ እንደሆነ ማወቅም ሆነ መጠበቅ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚያረካ ተግባር አይደለም፡፡ ይልቁንም  ውሻም ስጋ በል እንዲሆን ፈረስ ደግሞ የማያመሰኳ ሳር በል እንዲሆን ያስቻለው መሰረታዊ የአካል አደረጃጀትና አሰራርን (Anatomy and Physiology) ተግንዝቦ እነዚህን እንስሳት በተሻለ ሁኔታ ለመያዝ ማስቻል ነው፡፡ በሌላ በኩል የማህበረሰብ አገልግሎት በሚል መንግስት ከመደበው በጀት ቀንሶ ለአካባቢው ማህበረሰብ የተወሰኑ ሥራዎች መስራት ሃሳቡን ያሳንሰዋል፡፡ መንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ ወይም ዉሃ ብንሰራለት ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት የሰሩትን ደገምን እንጅ አዲስ ነገር ጨመርን ማለት አይሆንም፡፡ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የማህበረሰብ አገልግሎት ማለት ግን ዩኒቨርሲቲው ከጠበቀውና  ካመነጨው ዕውቀት እየጨለፈ በተግባር ለማህበረሰቡ አገልግሎት ሲሰጥና ችግር ሲፈታ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች አሁን በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በማህበራዊ ዘርፎች በአለም ላይ ለምናየው ልዩነት መሠረቶች ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ አሁን ላሉ ልዩነቶች መሠረት ተደርገው የሚወሰዱት የአውሮፖ የህዳሴ እንቅስቃሴ፣ የኢንዱስትሪ አብዮት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አብዮት፣ የናኖ ቴክኖሎጂና የባዮቴክኖሎጂ መሠረቶች ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው፡፡ የመንግስት አወቃቀርና አሰራርም ቢሆን በዩኒቨርሲቲዎች ተጽዕኖ አርፎበት በሂደት እየዳበረ የመጣ ነው፡፡ በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበረሰብ የሚያድግበትና በቀጣይነት እየበለፀገ የሚሄድበትን አግባብ ለመፍጠር ሳይታክቱ ሲሰሩ የነበሩና አሁንም እየሰሩ ያሉ ተቋሞች ናቸው፡፡

ታምራዊ የማህበረሰብ ለውጥ እንዲመጣ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱና አሁንም በመጫዎት ላይ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች የሚመሩት ምሁራኖቻቸውን በሳይንሳዊ ትንታኔ መሠረት እንዲመራመሩና በጥልቅ የሀሳብ ትንተና የሚገኘን ነገር በማስተማርና በማስረጽ የማህበረሰብ እድገት እንዲመጣ በመስራት ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት ዕውነታን የሚለዩት በተግባራዊ ውጤቱ ነው፡፡ አንድ ሀሳብ በተግባር ከሰራ ተቀባይነት ሲያገኝ በተግባር ካልሰራ ግን ማንም ያቅረበው ማን ውድቅ ይሆናል፡፡ ይህን መሠረት በማድረግና በማያቋርጥ የተግባር ፈተና በማለፍ ገሐዱን አለም መረዳት የሚያስችል ዕውቀት ከመፍጠራቸውም ባሻገር ዕውቀትን መሠረት ያደረገ ግዙፍ

ሀብት እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡ ዛሬ በሀብታቸው፣ በቴክኖሎጂያቸውና በወታደራዊ አቅማቸው የጠነከሩ ሀገሮች የጥንካሬያቸው መሠረት በዩኒቨርሲቲዎቻቸው መሪነት የጨበጡት የቴክኖሎጂ መሠረት ያለው ግዙፍ ሀብት ነው፡፡ ይህን ሀብት ቀጣይነት ባለው መልኩ አዳዲስ ቴክኖሎጂና አሠራር እንዲያመጣ ይጠቀሙበታል፡፡ በመሆኑም በትውልድ ቅብብሎሽ የሚገነባና የሚዳብር የማይነጥፍ የሀብት ምንጭ በዩኒቨርሲቲዎች እንደሚገነባ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ከዩኒቨርሲቲዎቿ ወደር የለሽ ጥቅም እያገኘች እንደሆነ የሚነገርላት ሀገር አሜሪካ ነች፡፡ ለምሳሌ ቦስተን የሚገኘው የማሳቹሴት የቴክኖሎጂ ተቋም እየተባለ የሚታወቀው ዩኒቨርሲቲ ያስመረቃቸው ምሩቃን ከ5000 በላይ ኩባንያ በመመስረት ከሚሊዬን በላይ ሰዎችን የስራ ዕድል በመፍጠር በአመት ከ230 ቢሊዬን የአሜሪካን ዶላር በላይ በሽያጭ እንደሚገኝ ይገመታል (See Engines or innovation, 2010)፡፡ ይህ ተቋም ከፍተኛ ወታደራዊ ጠቀሜታ ያለውንና አሜሪካ በሁለተኛው የአለም ጦርነት በለስ እንዲቀናት አስተዋጽኦ ያበረከተውን ራዳር የተባለ መሳሪያም በመፍጠርና በማሳደግ ይታወቃል፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን የትውልድ ቀረፃ፣ የቴክኖሎጂና የአዳዲስ ሀሳቦች መፍለቂያና የወደፊት መንገድ አመልካች በመሆን ዩኒቨርሲቲዎች ሚናቸው ትልቅ መሆኑን ብዙ መንግስታት ተገንዝበዋል፡፡ ይህን ሁኔታ በመገንዘብ በርካታ የአፍሪካ መንግሥታት ዩኒቨርሲቲዎቻቸውን ለማጠናከርና ለማስፋፋት እየሠሩ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም በአፍሪካ (ወደር የለሽ) ግንባር ቀደም እንዲሆኑ ዩኒቨርሲቲዎቿን የማስፋፋትና የማጠናከር ሥራ እየሠራች ነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ተቋቁመዋል፡፡ ያሉቱም እንዲጠናከሩ እየተደረገ ነው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም የዚህ አጠቃላይ ንቅናቄ አካል ነው፡፡

## 2. የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አፈጣጠርና ባህሪያት

የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአለማችን የተመሰረቱት ጀርመን ሀገር በ19ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ይነገራል፡፡ በወቅቱ ታዋቂ የነበሩት ምሁርና የሀገሪቱ የትምህርት መሪ ሁምበልት በዩኒቨርሲቲ ሊተገበሩ የሚገባቸውን ሶስት ቁልፍ መርሆች አስቀምጠው ነበር፡፡ እነዚህም፡-

ሀ. ምርምርና ማስተማር በኡደት የሚተገበሩና በመደጋገፍ የሚሰሩ የዩኒቨርሲቲ ተግባሮች መሆን እንዳለባቸው (የምርምርና የማስተማር ኡደት)፣

ለ. የአካዳሚክ ነፃነት (የመማርና የማስተማር ነፃነት)፣

ሐ ስነጥበብና ሳይንስ ላይ ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት፣

የሚሉ ናቸው፡፡ የሁምቦልትን ሀሳብ መሠረት ባደረገ መልኩ የበርሊን ዩኒቨርሲቲ እንዲቋቋም ስለተደረገ ሌሎችም የጀርመን ዩኒቨርሲቲዎች ይህን ልምድ በመውሰድ ሊጠናከሩና በአለማችን በዛን ወቅት ገናና ለመሆን ቻሉ፡፡ ይህ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ብለን የምንገልፀው ተቋም ዋነኛ መለያውም የምርምርና የማስተማር ስራዎች ኡደት ነበር፡፡ በመሆኑም የትምህርት መድረክ ተማሪና አስተማሪ በአንድ ላይ የሚማሩበትና የሚመራመሩበት እንጂ መምህሩ ቀድሞ ያወቀውን ብቻ ለመካፈል የሚመጡ ተማሪዎች የማይፈጠሩበት ሁኔታ ፈጠረ፡፡ በዚህ አሰራር ተማሪዎች በዕውቀት ፈጠራ ሂደት ያላቸውን ተሳትፎ አስፈላጊነት አጉልቶ ማውጣት ተቻለ፡፡ በዚህ ሂደት የሚወጡ አዳዲስ ዕውቀትና ቴክኖሎጂዎችን መጋራት የሚችልበት መድረክ በማስፈለጉ ሴሚናሮች፣ ስብሰባዎች፣ የምርምር መጽሔቶችና ሌሎች ተመሳሳይ መድረኮች እየተጠናከሩ መጡ፡፡ ይህ በሂደት እያደገ መጦ የብዙ ሀገሮችን ቀልብ በመሳቡ ብዙ የምዕራብ አውሮፖ ሀገሮችና አሜሪካ አሰራሩን ወደ ሀገራቸው ወስደው ተግባራዊ አደረጉት፡፡

የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገለፁባቸው ባህሪያት አሉ፡፡ በዋናነት መገለጫቸው ለምርምር ጥራት፣ ጥልቀት ተከታታይነትና ስፋት ያላቸው ቁርጠኝነት ነው፡፡ ብዙዎቹ የበለፀጉ ሀገራት ዕድገትና የዜጐችን ብልጽግና ለማረጋገጥ እነዚህን ተቋማት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀማሉ፡፡ እ.አ.አ በጥቅምት 2013 የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበር፣ የአውሮፖ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ማህበርና በቻይና ሀገር የሚገኙ የተወሰኑ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ዩኒቨርሲቲ መለያ ባህሪያቶችን በጋራ በመለየት እነዚህ ባህሪያት እንዲጠበቁላቸው የሚገለጽ

ሰነድ በጋራ አውጥተው ነበር፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ዋነኛ ባህሪያት ምንድን ናቸው የሚለውን በዚህ ሰነድ ላይ ለዩኒቨርሲቲያችን አቅጣጫ ከማስቀመጥ አንፃር መግለጹ ጠቃሚ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ዋና ዋናዎቹ የምርምር ዩኒቨርሲቲ መለያ ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ምርምር ለመስራትና ለማስተማር የቆረጡ ጥራት ያላቸው ምሁራን መኖር፣

ለ. ምርምርና ጥራት ያለው ትምህርት የሚካሄድበት መሠረተ ልማትና ተስማሚ ምሁራዊ ሁኔታ መኖር፣

ሐ. ለመመራመርና ለመማር ከፍተኛ ዝግጁነት ያላቸው ተማሪዎች መኖር፣

መ. ለምርምርና ጥራት ያለው ትምህርት አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭ መኖር ፣

ሠ. ራዕይ ያለውና አቅሙን የገነባ አመራር መኖር ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ዘርዘር ያሉ ጉዳዮችን ጠቅለል ባለ መልኩ አንድ የአለም ባንክ ያሰራው ሰነድ እንደሚከተለው ይገልፃቸዋል፡-

ሀ. ብቃት ያላቸው ምሁራንና ተማሪዎች በአንድ ዩኒቨርሲቲ መሰባሰብ፣

ለ. ራዕይ ያለውና በየጊዜው ራሱን የሚያበቃ (Visionary & Dynamic) አመራር (ተስማሚ የሆነ አስተዳደር) መኖር፣

ሐ. በቂ የሆነ መሰረተ ልማትና ግብዓት መገኘት፣

ሁሉም ስለምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገልጹ ፀሐፊዎች የሚያተኩሩበት ነጥብ ምርጥ መምህራንና ተማሪዎች የማግኘት ጉዳይን ነው፡፡ ዛሬ በአለማችን የሚገኙትን ዩኒቨርሲቲዎች የሚመሩት የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ከሁሉም የአለም ጫፍ አነፍንፈው አቅም ያላቸውን ምሁራንና ተማሪዎች በግቢዎቻቸው በመሰብሰብና ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የተገነቡ ናቸው፡፡ ዋናው ጥያቄ በኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ የምርጦች ምሁራን ስብስብ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንዴት መፍጠር ይችላል የሚለው ነው፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ት/ቤቶች ተምረው ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎችን በማብቃት እንዴት ጠንካራ የሀገር ኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ መሠረት መመስረት ይቻላል ነው ጥያቄው፡፡ እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን በመመለስ ለሀገሪቱ ፈጣን ልማትና ብልጽግና አስተዋጽኦ የሚያበረክት ምርምር ማበርከት የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግብ ነው፡፡ ይህንን ለማሳካትም የተለያዩ ስልቶችን መጠቀምና ውጤት ማስመዝገብም ይጠበቅበታል፡፡

## 3. የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጉዞ አቅጣጫ

ባሕር ዳር ሀገሪቱ በማኅበራዊ ሳይንስ፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግር የዳበረ ዕውቀትን በመፍጠር የተፈጠረውን ዕውቀት ወደተጨባጭ ሃብት ለመቀየር የሚችል ማህበረሰባዊ አቅም ለመፍጠር እንዲያስችለው የመረጠው አቅጣጫ ባለሰፊ መሰረት የምርምር ዩኒቨርሲቲ መሆንን ነው፡፡ ቀደም ባለው ክፍል በዝርዝር እንደተመለከተው የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ከሌላው ዩኒቨርሲቲ ለየት ያሉ ባህሪያት ያሏቸው ሲሆን እነዚህ መገለጫዎች በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሂደት እየጎሉ እንዲመጡ የሚያደርግ እርምጃን ይጠይቃሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ አመታት ትኩረት ሰጥቶ የሚያከናውናቸው ተግባራት ተጨባጭ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ገጽታ የሚያላብሱት ይሆናል፡፡ እነዚህ ዩኒቨርሲቲው የሚላበሳቸው ገጽታዎች የሚከተሉትን ወሳኝ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ባህሪያት የሚያካትት ይሆናል፡፡

የጉዞ አቅጣጫ የሚሰነው መዳረሻ ግብን በመለየት ነው፡፡ መዳረሻ ግቡ የምርምር ዩኒቨርሲቲ መገንባት ከሆነ ተቋሙ በመጨረሻ ላይ የሚኖረውን መሰረታዊ ገጽታ በግልጽ በማስቀመጥ የሚታቀዱና የሚከናወኑ ስራዎች ሁሉ ወደዚሁ ግብ የሚወስዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ይሆናል ሲባል የሚቀጥሉት ገጽታዎች የተላበሰ ይሆናል ማለት ነው፡፡

### 3.1. ምርጥ ተመራማሪና ምርጥ አስተማሪ የሞሉበት ተቋም መሆን

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን አብዛኛው መምህራን ምርጥ ተመራማሪና አስተማሪ ይሆናሉ፡፡ ይህ ማለት ቢያንስ 50% የሚሆኑት መምህራን የፒ.ኤች ዲግሪ ያላቸውና በተማሩበት የትምህርት መስክ ምርምር የሚያካሂዱና የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የሚያማክሩ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አሁን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያሉት 200 የሚሆኑ ረዳት ፕሮፌሰርና ከዚያ በላይ ማዕረግ ያላቸው መምህራን ቁጥር ወደ 800 ከፍ ይላል ማለት ነው፡፡ የአካዳሚክ ማዕረግ ተገኝቶም የመቆም ሁኔታ ስለሚያጋጥም ለዚህ መስፈርት የምንፈልገው ማዕረግ መድረሳቸውን ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ባለው መልኩ ምርምር የሚሰሩ መሆናቸው ይሆናል፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርጥ ተመራማሪና አስተማሪ የሆኑ መምህራን ሲኖሩት መገለጫዎቹ የሚከተሉት ነጥቦች ናቸው፡፡

- በርካታ መምህራን በብዙ ፕሮጀክቶች የመሳተፍ ሁኔታ መኖር፣

- በርካታ መምህራን በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዩች አስተያየት እንዲሰጡ በታዋቂ የመገናኛ ብዙኃን መጋበዝ፣
- ብዙ ቁጥር ያላቸው መምህራን ለራሳቸው ፈጠራ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማግኘት መቻል፣
- በርካታ ዕውቀት የሚጨምሩና ችግር ፈቺ የሆኑ መጽሐፍትና የኅትመት መጽሔቶች ላይ የመምህራን ተሳትፎ ጉልህ ሆኖ መገኘት፣
- በሙያ መስካቸው የራሳቸውን ኩባንያ የሚያቋቁሙ መምህራን ቁጥር መጨመር@
- የሚያስተምሩትን ትምህርት ራሳቸው ተመራምረው ባገኙት ውጤት በመደገፍ የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር ማደግ(50% ሆኖ መገኘት)፣
- 50% የሚሆኑት መምህራን የድኅረ ምረቃ ተማሪዎችን ማማከር መቻል፣
- 50% የሚሆኑት መምህራን ቢያንስ በዓመት አንዴ በታወቀ የምርምር ስብሰባ መሳተፍ መቻል ናቸው።
- በማህበራዊ ተሳትፎ በፈቃደኝነት ነጻ ሙያዊ አገልግሎት የሚሰጡ መምህራንና ተመራማሪዎች ቁጥር ማደግ እና በሙያ ማህበራት ያላቸው ተሳትፎ መጠናከር፣
- ከስር የሚከተሏቸው በርካታ ተማሪዎች ኑረው በሙያ መስካቸው በማንኛውም ጊዜ የሚጠየቁ፣ መልስ መስጠት የሚችሉና (Experts & Professionals) የራሳቸውን የሙያ ኢምፓየር መገንባት መቻል ነው።

## 3.2. ደረጃውን የጠበቀ ምርምርና ትምህርት መስጠት የሚያስችል መሰረተ ልማትና ግብአት መኖር፣

የምርምር ዩኒቨርሲቲ በመሠረታዊነት የሚፈልጋቸው ግብአቶችን ማሟላት ወሳኝ ጉዳይ ነው። የምርምር ዩኒቨርሲቲ በጣም ውድ የሆነ ተቋም ነው። ብዙ መዋለ ንዋይ የሚጠይቅ ግብአት ይፈልጋል። ከዚህ በመቀጠል የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ሊኖር የሚችለው የግብአት ገጽታ ቀርቧል።

### 3.2.1. የምርምር በጀት

የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለምርምር የሚመድበው በጀት ትልቅ ነው። በአሁኑ ወቅት ምርጥ የሚባሉ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የአመት የምርምር በጀት ከቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር በላይ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካን ሀገር የሚገኘው የሚችጋን ዩኒቨርሲቲ እ.አ.አ መስከረም 2011

በሰጠው መግለጫ በዛን ወቅት ለምርምር የመደበው በጀት 1.24 ቢሊዬን የአሜሪካን ዶላር ነበር፡፡

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር በጀትን በፍጥነት የማሳደግ ጉዳይ ወሳኝ ስራ ነው፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ስንሆን አሁን ያለን የበጀት ሁኔታ መዋቀራዊ ለውጥ ይኖረዋል፡፡ አሁን የግንባታ በጀታችን የገነነውን ያህል የምርምር ተቋም ስንሆን የምርምር በጀታችን የመሪነቱን ሚና ይወስዳል ማለት ነው፡፡

የምርምር በጀቱ ሲያድግ የምርምር መሠረተ ልማቶች (ምርምር፣ ቤተ-ሙከራዎችና ሌሎች ምርምርን የሚያሳልጡ ነገሮች) እና የምርምር ተግባሮችን መፈፀም የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ወቅት ሁሌም የሚሰሩና የድህረ ምረቃ ተማሪዎችና እንደ አግባብነቱ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎችም የሚራወጡባቸው የምርምር ቤተ-ሙከራዎችና የምርምር መድረኮች ይኖሩናል ማለት ነው፡፡ አድባቡ በአብዛኛው ምርምር ላይ መወያየት፣ መከራከርና መስራት ላይ ያተኩራል፡፡ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር በጀት አሁን ካለበት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ በደረጃ በማሳደግ በጀቱን 40% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

የምርምር በጀት ባደገ ቁጥር ገበያ ላይ የሚገኝ የምርምር መሳሪያ በመግዛት ብቻ ትልቅ ይኮናል ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ የምርምር መሰረተልማትና ግብዓትን በተለይም መሳሪዎችን በበጀት ተደግፎ ለመግዛትና ለመመራመር ከማሰብ ይልቅ በራስ ለመፍጠር ማቀድ ተገቢ ነው፡፡ የምዕራቡ ዓለም ዩኒቨርሲቲዎች የሚመራመሩበትን መሳሪያ የሚፈጥሩት ራሳቸው ናቸው፡፡ በራስ በተፈጠረ መሳሪያ መመራመር ከተቻለ ግኝቱ በአብዛኛው አዲስና በሳይንስ ማማ ላይ የሚያስቀምጥ ይሆናል፡፡ በመሰረቱ ዩኒቨርሲቲዎች ከቮኬሽናልና ከቴክኒክ ትምህርት ቤቶች የሚለዩትም በዚህ ሳቢያ ነው፡፡

### 3.2.2. የምርምርና ጥራት ያለው ትምህርት መስጫ ሌሎች ግብዓቶች መሟላት

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን አለምአቀፍ ደረጃ ያሏቸው ቤተ ሙከራዎችና ቤተ መጽሃፍት ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ዓመታት የምርምር ማዕከላትን ዘመኑ በደረሰበት የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲደራጁ ማድረግ ትኩረት የሚሰጥበት ይሆናል፡፡ በመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚኖራቸውን ግብዓቶች ከቤተሙከራዎች ጋር የማሟላት ሥራ ይከናወናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲውና ሌሎች

የግል ኩባንያዎች በጋራ የሚሰሩባቸው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ፓርኮች እንዲኖሩ ትኩረት በመስጠት የሚሰራ ይሆናል።

### 3.2.3. ጥራት ያላቸውና ለመማርና ለመመራመር የሚተጉ ተማሪዎች ይኖራሉ

የምርምር ዩኒቨርሲቲ አንዱ መገለጫው መማር፣ ሀሳብ መለዋወጥ፣ መመራመር የራባቸውና አቅም ያላቸው ተማሪዎች የሚጐርፉበት ተቋም መሆኑ ነው። አለምን እየመሩ ያሉት ዩኒቨርሲቲዎች ዋነኛው የጥንካሬ ምንጫቸው በአለም ላይ ለመማርና ለመመራመር የሚተጋ ዜጋን ሁሉ የሚስቡ መካዎች መሆናቸው ነው። ጥራት ያለው ተማሪ ወስደው የራሳቸውን ሂደት ሲጨምሩበት ወደር የለሽ ውጤት ያገኛሉ።

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሚሰጠው ትምህርትና ምርምር በጣም ጥሩ ከሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ጉበዝ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ለመማር ፍላጐት ይኖራቸዋል። ጉበዝና ታታሪ ተማሪ የሚሳበው ጥራት ያለው መምህር ሲያይ ነው። በሀገራችን የሀይማኖት ተማሪዎች የታወቀ ሊቅ ፍለጋ ወንዝ አቋርጠው ፈልገውና አፈላልገው እንደሚያገኙና እንደሚሰባሰቡ ሁሉ ዩኒቨርሲቲያችንም ምርጥ መምህራንን ጉበዝ ተማሪዎችን ለመሳብ እንደ ማግኔት መጠቀም ይገባዋል።

በተለይም የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ለመመልመል የሚያስችል አቅምና ፍላጐቱ ያላቸው እንዲመጡና ምርምሩን እንዲያሳልጡ የሚሆንበት አግባብ ይኖራል። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን የተማሪዎቹ ሁኔታ በሚቀጥለው መልኩ ገጽታው ይቀየራል።

- 50% የሚጠጋው ተማሪ የድህረ ምረቃ ተማሪ ይሆናል።
- ቢያንስ ወደ 100 የሚጠጉ የፒ.ኤች ዲግሪ ተማሪዎች ከሃያ የተለያዩ የትምህርት መስኮች በአመት ይመረቃሉ፣
- የምርምር ሥራ ላይ ከፍተኛ የሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ ይኖራል።

### 3.2.4. የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመመስረት የቆረጠና ግልጽ ራዕይና ስትራቴጂ ያለው አመራር መኖር

የምርምር ዩኒቨርሲቲ ያለ የዩኒቨርሲቲው አመራር ቁርጠኝነትና ትጋት የሚገነባ ተቋም አይደለም። ጠንካራ የምርምር ዩኒቨርሲቲ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚገነባ ተቋም ነው። በመሆኑም አንዱ በሰራው ላይ እየተመሰረቱና እያዳበሩ የሚገነባ ተቋም ነው። የሚጠይቀውም ቁርጠኝነትና መስዋዕትነት ከባድ ነው። ለመሆኑ የምርምር ዩኒቨርሲቲን የሚመሩ ጥሩ የሚባሉ

አመራሮች መገለጫቸው ምንድን ነው ብለን መጠየቅና ምላሽ መስጠት ከአመራር አንፃር ያለንን አቅጣጫ በሚገባ ያሳያል። በመሆኑም የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመመስረት የቆረጠ አመራር መገለጫዎቹ፡-

- ሁሉም ስራዎቹ ምርምርና ማስተማርን በሑደት ከመፈፀም አንፃር ያላቸውን ፋይዳ ይገነዘባል፣
- ጥራት ያለው ምርምርና ማስተማር ለሚሰሩ መምህራን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በርትቶ ይሰራል። መምህራኖችንም በልዩ ሁኔታ ይከታተላል፣
- ብቃት ያላቸው መምህራንና ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲውን እንዲቀላቀሉ ተግቶ ይሰራል፣
- ከፍተኛውን መዋለ ንዋይ ምርምር ለማሳለጥና በምርምር የተደገፈ ትምህርት እንዲሰጥ ይመድባል፣
- ምቹ የምርምር፣ የማስተማርና በአጠቃላይ የምሁራዊ ከባቢ እንዲፈጠር ይሰራል፣ ያበረታታል፣ ስርአትም ይዘረጋል፣
- የድህረ ምረቃ ፕሮግራም በልዩ ሁኔታ እንዲጠናከር ይጥራል፣
- የምርምር ህትመቶች ስፋት፣ ጥልቀትና ጥራት እንዲሻሻል በልዩ ሁኔታ ይከታተላል።
- በውስጥም ሆነ በውጭ የአካዳሚክ ነፃነትን ለማስከብር የሚያስችል ጠንካራና ሞገስን የተላበሰ ( Charsmatic)ስብዕና ያለው እንዲሆን ራሱን ይገነባል።

# 4. የጉዞ አቅጣጫችን የተመረጠበት ምክንያቶች

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ መሆን አለብኝ ብሎ የመረጠው የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚሰጠውን ከበሬታ ለማግኘትና ለመኩራራት አይደለም። ተግባር ላይ በማይውልና በትርኪ ምርኪ የህትመት ጋጋትም ቤተ-መጽሐፎችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጠረጴዛም ለማጨናነቅ አይደለም። ዋናው ምክንያት በሀገራችን ቀጣይነት ያለው ልማት ተረጋግጦ ህዝቦቿ እንደሌሎች የበለፀጉ ሀገሮች ህዝቦች ተስማሚና ጤናማ ኑሮ እንዲኖሩ ለማድረግ በሚደረገው ርብርብ የኛን አስተዋጽኦ ጠንካራ ለማድረግ ነው። ቀደም ባለው የዚህ ጽሁፍ ክፍል ላይ እንደተገለጸው የቴክኖሎጂ መሠረት ያለው ሀብት የማፍራት ተግባር ላይ በአብዛኛው የመሪነቱን ሚና የተጫወቱት የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች እንደሆኑ አይተናል። የመንግስትንም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን አደረጃጀት፣ አሠራርና አጠቃላይ ሁኔታ በዋናነት መሰረታቸው የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ያፈለቋቸው ሀሳቦች እንደነበሩም አሰተውለናል። አሜሪካ ውስጥ ያለ አንድ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ያፈራቸው ምሩቃን ከ5000 በላይ ኩባንያ በማቋቋም ከ230 ቢሊዮን ዶላር በላይ በአመት በሽያጭ ማስገኘት የሚያስችሉ ተቋሞች መመስረት እንደቻሉ አይተናል። ይህ በአንድ ተቋም ስራ የተፈጠረው ሀብት የሀገራችንን የአመት አጠቃላይ በትልቁ የሚበልጥ ሀብት ነው።

የኛን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ያደረጉ የወደፊት የሀገራችን ኩባንያዎችን የሚፈጥሩ ኢትዮጵያውያንን ለማፍራት ነው የምርምር ዩኒቨርሲቲ መሆን የመረጥነው። ለዘመናት ተንሰራፍቶ ያለውን ድህነት በመማር፣ በማስተማር፣ ጥልቅ ምርምርና ትንተና መሠረት ባደረገ አሠራርና አደረጃጀት መሠረት ለማስወገድ የሚያስችሉ ትጥቆችን ስለሚያስታጥቀን ነው አቅጣጫችንን የመረጥነው። ትምህርት ተምሬ የገጠሩን አስከፊና አስቸጋሪ ህይወት እላቀቃለሁ ማለቱ ቀርቶ በምማረውና እኔም ተመራምሬ በማገኘው ዘዴ የገጠሩን ሁኔታ እቀይራለሁ የሚል ወጣት ለማፍራት ነው የምርምር ዩኒቨርሲቲ መሆን የመረጥነው።

በአጠቃላይ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመሆን አቅጣጫ የያዝነው የሚከተሉትን ጭብጦች መሠረት አድርገን ነው።

- መምህራኖቻችንና ተማሪዎቻችን ላይ ዕውቀት፣ ክህሎትና አጠቃላይ የአመለካከት ዕድገት በማምጣት አካባቢያቸውን፣ ሀገራቸውንና አለምን የተገነዘቡ አምራች ዜጎች ለማድረግ፣

- ምሁራኖቻችንና ተማሪዎቻችን ውስጥ ያለውን ዕውቅትና ክህሎት ወደ ሀብትነት መቀየር የሚያስችል ሁኔታ በመፍጠር የቴክኖሎጂ መሠረት ያለው ሀብት በብዛትና በጥራት እንዲገኝ ማድረግ የሚያስችል አቅም ለመገንባት፣
- ትምህርት ለማህበረሰብ ዕድገት መሠረት የሚሆንበትን ሁኔታ በተግባር ለማሳየት፣
- ዕውቀት፣ ክህሎትና ፈጠራ ያለው ባህር ማዶ ብቻ ነው የሚለውን አስተሳሰብ በማስቀረት፣ መነቃቃት ፈጥሮ የራስ መተማመን ለመፍጠር፣
- በተከታታይ ትውልዶች የሚገነባ የዕውቀት፣ የቴክኖሎጂና የሀብት መሠረት የሚጣልበት አግባብ ላይ አስተዋጽኦ ለማድረግ፣

በአጠቃላይ ለኢኮኖሚ፣ ለፖለቲካና ለማህበራዊ ዕድገት አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነ ተቋም የመፍጠር ፍላጐት ነው የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚለውን እንድንመርጥ ያደረገን።

## 5. ወደመረጥነው አቅጣጫ የሚወስዱን ስልቶች

ይህ ክፍል የምርምር ዩኒቨርሲቲ እንድንሆን የሚያበቁንን ስልቶች የምናይበት ክፍል ነው፡፡ የምንሄድበትን አቅጣጫ በሚገባ ከላይ ገልፀናል፡፡ ገጽታዎችም ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ አስቀምጠናል፡፡ ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ በምን ዓይነት ስልቶች ግባችንን እናሳካለን የሚለውን ጥያቄ በየመገለጫዎች ሥር ማስቀመጡ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም በሚከተለው አግባብ አስቀምጠናቸዋል፡፡

### 5.1. ምርጥ ምሁራን በበቂ ሁኔታ የምንፈጥርበት አግባብ

#### ሀ. አሁን በሥራ ያሉ መምህራንን የምናበቃበት አግባብ

በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ያሉት በርካታ መምህራን አቅማቸው በሚፈለገው ደረጃ አይደለም፡፡ በየወቅቱ የሚከሰተውን የመምህራን ፍላጐት ለማርካት ብዙም ጥንቃቄና ራእይን መሠረት ባደረገ አግባብ ቅጥር ባለመፈፀሙ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሊኖረው የሚገባውን አይነት ቁመና ላይ ያሉ መምህራን በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን በርካታ መምህራን ማብቃት ይገባል፡፡

አሁን በሥራ ላይ ያሉ መምህራንን የምናበቃባቸው ስትራቴጂዎች የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች፣ አጫጭር ስልጠናዎችና በምርምር መድረኮች ላይ ያለ ተሳትፎ በመጨመር የሚሉትን ያካተተ ነው፡፡ የረጅም ስልጠናዎች የሚያካትቱት በ2ኛና በ3ኛ ዲግሪ በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ማሰልጠንን የያዘ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በልዕቀት ማዕከል አትኩሮ በሚሠራባቸው መስኮች ከዩኒቨርሲቲው ውጭ በአለም ላይ ባሉ ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች ልኮ ማስተማርን ያካተተ አቅጣጫ እንከተላለን፡፡ ይህን ለመፈፀም ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ውጭውን በሙሉ በመሸፈን እስከማሰልጠን የሚደርስ ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡

አጫጭር የመምህራን የአቅም ግንባታ ሥራዎች የሚያተኩሩት የመምህራኖቻችንን የቋንቋ፣ የምርምር፣ የቴክኒክ ብቃቶች በማሳደግ ላይ ነው፡፡ አጫጭር ስልጠናዎች በመምህራኖቻችን ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት እና እነዚህን ክፍተቶች በመሙላት ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ፡፡ መለኪያውም በስልጠናው ያለፉ መምህራን በተጨባጭ የሚያሳዩት የተገነባ አቅም ነው፡፡

በሥራ ላይ ያሉ መምህራን በተለያዩ የምርምር መድረኮች እንዲሳተፉ ማድረግ ሌላው ተግባር ነው፡፡ በየትምህርት ክፍሉ በሚዘጋጁ፣ በፋኩልቲና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚዘጋጁ የምርምር መድረኮች በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል፡፡ በራሳቸው የሰሩት የምርምር ሥራ ከሌላቸው

ሌሎች የሠሩትን የምርምር ሥራ ከልሰው እንዲያቀርቡ በማድረግ ምርምር የመሥራትና የማሥተማር አቅማቸውን መጨመር ይቻላል፡፡ በመምህራን መካከል የፈጠራ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ ምንም አይነት በጀት ሳይመድብላቸው የፈጠራ ሥራ ካቀረቡ፣ ፈጠራቸውን ዩኒቨርሲቲው ለራሱ በነፃ እንዲጠቀምበት ወይም ለሶስተኛ ወገን የሚሸጥበት አግባብ ሲኖር መምህራኑ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሥርዓት መፍጠር ተገቢ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ዩኒቨርሲቲው የምርምር በጀት መድቦ አዲስ ፈጠራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራና በዩኒቨርሲቲው ባለቤትነት ቴክኖሎጂውን ወደ ሀብትነት የመቀየር ስልትም ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## ለ. ምርጥ መምህራን በቅጥር ማሟላት

ይህ አዲስ መምህር የመቅጠር ስትራቴጂ በጥንቃቄና የዩኒቨርሲቲውን ራእይ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም በቅጥር ወቅት ዋነኛው የመቅጠሪያ መሥፈርት ምርምር የመሥራት አቅምን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት መምህር ሊቀጥሩ የሚፈልጉ ትምህርት ክፍሎች ዕጩዎች ሲመረቁ በተለይም በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ላይ የሠሩትንና ሌሎች የህትመት ሥራዎች ላይ ያላቸውን ውጤት በሚገባ መፈተሽ ይገባቸዋል፡፡

በመጀመሪያ አዲስ የመምህራን ቅጥር ሊያተኩር የሚገባው ከምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የተመረቁ ምሁራንን በመብራት ፈልጎ ሲገኙ የሚቀጠሩበትን አግባብ መፍጠር መሆን ይኖርበታል፡፡ በተለይ ከምዕራባዊያን ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የተመረቁ ምሁራንን በልዩ ሁኔታ ስቦ የመቅጠር አቅጣጫ መከተል ተገቢ ነው፡፡

በአጠቃላይ አዲስ የምሁራን ቅጥር ብቃትን መሠረት ያደረገ ልዩ ፍለጋ በማከናወን የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ተቋማት ምሁራን ሲመረቁ ልዩ ክትትል በማድረግ ልዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ሥርዓት ዘርግቶ ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመመሥረት እርሾ የሚሆኑ ምሁራንን ማሰባሰብ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ በማያያዝም መቅጠሩ ብቻ በቂ ባለመሆኑ በራዕዩ ሃዲድ ሊጓዝ እንዲችል ማብቃት ይገባል‹‹ በመሆኑም የተቀጠረው ሰው ላይ በተከታታይ ተጨማሪ የአቅም ግንባታ ይደረግለታል፡፡ በቀጣይም የብቃት ማረጋገጫ ግምገማዎች የሚተገበሩበት ስርዓት ይፈጠራል፡፡

### ሐ. በወቅታዊና ለአጭር ጊዜ ቅጥር መምህራንን ማሟላት

በነባር መምህራንና በቅጥር ሊሟሉ የማይችሉ የምሁራን ቦታዎችን በወቅታዊነት በቅጥር ማሟላት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ስትራቴጂ ምርጥ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ተቋማት የሚሠሩት ምሁራን ለአጭር ጊዜ መጠው ከነባር መምህራን ጋር ወይም በራሳቸው እንዲሰሩ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህ በጊዜያዊነት የመቅጠር አቅጣጫ ወቅታዊ ክፍተቶችን ከመሙላት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከነባር መምህራኖቻችንና በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር የምርምርና የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሠሩ ማድረግን ያለመ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የጋራ ፕሮጀክት የሚቀርፁበትን አግባብ በትኩረት መሠራት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ የዳበረ የማስተማር፣ የመመራመርንና ፕሮጀክት የመቅረጽን አቅም ማስተላለፍን በግብ መያዝ ይገባዋል፡፡

### መ. የውጭ መምህራን ቅጥር

በዩኒቨርሲቲያችን ያለውን ጥራት ያላቸው መምህራን የማግኘት ችግር በሃገር ውስጥ ሚገኝ የሠው ኃይል መፍታት ከአጭር ጊዜ አኳያ ፈታኝ በመሆኑ ችግሩን የምንፈታበት ሌላው መንገድ የውጭ መምህራን በመቅጠር ነው፡፡ የውጭ መምህራን ስንቀጥር በታወቁ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የሠሩት ላይ በማተኮር ይሆናል፡፡ ምርምር የመሥራትና ፕሮጀክት የመንደፍ አቅም ያላቸውን መምህራን በልዩ ትኩረት መፈለግ ይገባል፡፡ ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓታችንን ተከትለን የውጭ መምህራን ፍለጋችንን መሥራት ትኩረት የሚሻ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡

## 5.2. ምርጥ ተማሪዎችን የምናገኝበት አግባብ

ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚገነባው በምርጥ ምሁራን ስብስብ ብቻ አይደለም፡፡ የምርጥ ምሁራን ስብስብን እንደ ዋነኛ መሳቢያ በመጠቀም ምርጥ የቅድመ ምረቃና የድህረ-ምረቃ ተማሪዎችን መሳብ ይገባል፡፡ በዩኒቨርሲቲያችን ምርጥ ተማሪዎችን የምንስብበት አቅጣጫዎች የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል፡፡

### ሀ. የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ የተማሪዎች በገበያ ተፈላጊነት መጨመር

እንደሚታወቀው የሀገራችን ዜጐች ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የሚመጡት በገበያ የሚሸጥ ዕውቀት፣ ክህሎትና አጠቃላይ ስብዕና ለመገንባት በመሻት ነው፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው ውሰጥ

ከመግባታቸው በፊትና ገብተው በቆይታቸው ውስጥ ያካበቱትን አቅም በሚገባ እየፈተሹ ተከታታይነት ባለው መልኩ የምንሰጠውን የሰው ሀይል ግንባታ የተሳካ ማድረግ ይገባል፡፡ ከዩኒቨርሲቲው የተመረቁ ተማሪዎች የሚመዘኑት በተነፃፃሪ መልኩ በገበያ ላይ ያላቸው ተፈላጊነት፣ ከተቀጠሩ በኋላ አፈፃፀማቸውንና በራሳቸው የቀሰሙትን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ተጠቅመው ወደ ሀብትነት የቀየሩትን በሚገባ በመከታተል ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት የምሩቃኖቻችንን አጠቃላይ አፈፃፀም በሚገባ ፍትሾ ያለንን ውጤት መሠረት በማድረግ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች እየሄዱ ስለ ዩኒቨርሲቲው ገለፃ ማድረግ ይገባል፡፡ የዚህ ሥራ መሠረቱ ከዚህ ቀደም ያስመረቅናቸው ተማሪዎች ተጨባጭና እውነተኛ ይሆናል

በዩኒቨርሲቲው ውስጥም በምርምር፣ በፈጠራና በማህበረሰብ አገልግሎት ተማሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ተፈላጊነታቸውን መጨመር ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ወደ ሀብትነት ሊቀየሩ የሚችሉ ሀሳቦችን እንዲያመጡና ወደ ተግባር የሚለወጡበትን አግባብ መፍጠር ወሳኝ ነው፡፡ የተማሪዎችን የመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ተሳትፎ በመጨመርና ሳቢ እንዲሆን በማድረግ ምርጥ ተማሪዎችን የመሳብ አቅም ይኖረናል፡፡

### ለ. የተማሪዎች አገልግሎት አሰጣጥን አርኪ ማድረግ

ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች (መኝታ፣ ምግብ፣ ክሊኒክ፣ መዝናኛ፣ ምክር) ተማሪዎችን በሚያረካ መልኩ ለመስጠት የሚያገለግል አቅም መገንባት ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ግንባታ ቀጥሎ ትኩረት የሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአገልግሎት አሰጣጡ የላቀ ሆኖ መገኘቱ ምርጥ ተማሪዎችን ለመሳብ በወሳኝነት የሚያግዘው መሆኑ አይቀርም፡፡

### ሐ. አለማቀፋዊነት ልምድ እንዲያገኙ የማድረግ አቅጣጫ

ተማሪዎቻችን አለማቀፋዊ ልምድ እንዲያገኙ ማድረግ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ወሳኝ ጠቀሜታ ያለው ተግባር ነው፡፡ የነገ ተመራቂዎቻችን ስኬታማ መሆን የሚችሉት አለማቀፋዊ ልምዳቸው ጠንካራ ሲሆንና የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ጋር መስራት የሚችሉ ሲሆን ነው፡፡ በመሆኑም ይህ አቅጣጫ በተግባር የሚፈፀመው የሌሎች ሀገራት ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲያችን መጠው ከተማሪዎቻችን ጋር እንዲሰሩ በማድረግና የኛ ተማሪዎች ወደሌላ ሀገር ሄደው ልምድ እንዲቀስሙ በማድረግ ነው፡፡ ይህን ለማሳለጥ የአለማቀፍ ተማሪዎች ማዕከል በዩኒቨርሲቲያችን ማቋቋም ይገባል፡፡

መ. ምርጥ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን በመጠቀም ምርጥ ተማሪዎችን መሳብ

በምርምር ዩኒቨርሲቲ ምርምር በወሳኝነት የሚሠራው በድህረ ምረቃ ተማሪዎች ፈፃሚነትና በምርጥ መምህራን አማካሪነትና መሪነት ሑደት ነው፡፡ ችግር ፈችና በፋይናንስ የታገዘ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመንደፍና ተማሪዎችን በምርምር ስራ በስፋት በማሳተፍ ለሚሠሩ የምርምርና የፈጠራ ፕሮጀክቶች ዩኒቨርሲቲው ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ምርጥ የምርምር ቡድን ወይም ማዕከል በመገንባት ከነዚህ ማዕከላትና ቡድኖች የሚመረቁ ተማሪዎችን ብቃት እንደ ዋነኛ ምርጥ የተማሪ መሳቢያ ስልት ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም ተማሪዎች የምርምር ገንዘብ በመመደብና በተለይ ዩኒቨርሲቲው በልዩ ትኩረት ሊመራመርባቸው ባሰባቸው መስኮች ተማሪዎች የድህረ ምረቃ ቴሲሳቸውን እንዲሰሩ በማድረግ "በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ" መተግበር ይቻላል፡፡ ይህ ልንከተለው የሚገባ አቅጣጫ ነው፡፡

## 5.3. መሠረት ልማት ማሟላት

የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚጠይቃቸው መሠረተ ልማቶች ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ነገር ግን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር እነዚህ ግብዓቶች የሚወጣባቸው ወጭ ምክንያታዊ ነው፡፡ በምርምር ዩኒቨርሲቲ ወሳኝ ግብዓቶች ተብለው የተለዩ የመሠረተ ልማት ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. የምርምር ቤተ-ሙከራዎችን መገንባትና ማደራጀት

ዩኒቨርሲቲው በወሳኝነት መገለጫ ይሆኑኛል ብሎ በለያቸው የምርምር መስኮች የምርምር ቤተ-ሙከራዎችን የማሟላት ሥራ በከፍተኛ ትኩረት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ እነዚህ ቤተ-ሙከራዎች በታወቁ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ካሉ መሰል ቤተ-ሙከራዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑና እነሱንም እንደ ምሳሌ በመውሰድ በዛ አቅጣጫና ደረጃ መሠረት የሚደራጁ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በውሃ፣ በኃይል፣ በባዩቴክኖሎጂና በስነህዋ ሳይንስ አለማቀፍ ደረጃ ያላቸው ቤተ-ሙከራዎች መመሥረት ይገባል፡፡ ከምርምር ማዕከላት ቤተ-ሙከራዎች ማሟላት በተጨማሪ የምርምር ቡድኖች የሚፈልጓቸውን የምርምር ቤተ-ሙከራዎች ማሟላት ተገቢ ነው፡፡ በተለይም የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን የምርምር ቤተ-ሙከራዎች ማሟላት በትኩረት የሚሰራበት ይሆናል፡፡

የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች፣ የምርምር ማዕከላትና የምርምር ቡድኖችን ቤተ-ሙከራ ከማሟላት በተጨማሪ በቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞች የመማር ማስተማሩን የሚያግዙ ቤተ-ሙከራዎችን

በማሟላት ሂደት ለትምህርት ጥራቱ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ሁሉንም የቤተ-ሙከራ ግብዓቶችን ለማሟላት ትኩረት የሚሻው ጉዳይ መገንባቱና በቁሳቁስ ማሟላቱ ብቻ ሳይሆን በቀጣይነት መሳሪያዎቹ እንዲሠሩ ለማድረግ የሚያስችል የአስተዳደርና የቴክኒክ ዕውቀት ግንባታ ጉዳይ ይሆናል፡፡

### ለ. የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማሟላት

የምርምር ዩኒቨርሲቲ ጠንካራና አስተማማኝ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረት ልማት ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ጠንካራና አስተማማኝ የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት የጀርባ አጥንት በሚገባ ሊገነባ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር የዘመኑ ቴክኖሎጂ ያፈራውን ቁሳቁስ በማሟላት የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚጠይቀውን መሠረት ልማት ማሟላት ተገቢ ነው፡፡ የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ቁሳቁስ ከተሟላ በኋላ ቁሳቁሱን ከመጠቀም አንፃር ልንተገብር የሚገባንን ሶፍቴዎሮች ተግብረን ዩኒቨርሲቲውን ኢ-ዩኒቨርሲቲ የማድረግ ራእያችንን ለማሳካት ጠንክረን መሥራት ይጠይቃል፡፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተደራሽነት፣ ጥራትንና አግባብነትን ባረጋገጠ መልኩ ማሟላትም ወሳኝ ሥራ ነው፡፡

### ሐ. የዘመኑን ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረጉ የቤተ-መፃህፍት መሠረት ልማት ማሟላት

የምርምር ዩኒቨርሲቲ አንዱ መለያ ባህሪው የዘመኑን ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረጉና ወቅታዊ መፃህፎች፣ ህትመቶችና የምርምር ውጤቶች የሚገኙባቸው ቤተ-መጽሐፍቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የመምህራኖቻችንና የተማሪዎቻችን ፍላጐት መሠረት ባደረገ መልኩ እነዚህን ቤተ-መፃፍት መገንባት፣ በበቂ ሁኔታ ማደራጀትና መምራት የግድ ይለናል፡፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረት በማድረ በድረ-ገጽ ላይ የሚገኙ ህትመቶችና ጽሑፎችን መምህራንና ተማሪዎች በቀላሉ እንዲያገኙት ማድረግ የሚያስችል አሰራርም መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

### መ. ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ህንፃዎች መገንባት

የምርምር ዩኒቨርሲቲ ከሚሠራቸው ሥራዎች ልዩ ባህሪ አንፃር የህንፃ ግንባታዎቹ ራእዩን መሠረት ባደረገ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመምህራን ቢሮ፣ መማሪያ ክፍል ወዘተ. ሥራዎቹን መሠረት ባደረገና የምርምርና የሥልጠና መስኮችን መሠረት ባደረገ መልኩ ይገነባል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የመማሪያ፣ የቢሮ፣ የመኖሪያ፣ የመዝናኛ፣ የጤናና የስብሰባ ህንፃዎችን በተገቢው ሁኔታ መገንባት ይጠይቃል፡፡

### ሠ. መጠነ ሰፊ የሆኑ ገቢዎችን መፍጠር የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር

የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚጠይቀው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ይህን ከፍተኛ መዋለ ንዋይ ከመንግስት ካዝና ብቻ ሊሟላ አይችልም፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የራሱን የሀብት ምንጮች በመፍጠር ሰፊ የሆነ ገቢ ማግኘት ይገባዋል፡፡ በዚህም መሠረት በጥናት ላይ ተመስርቶ ለዩኒቨርሲቲው የሀብት ምንጭ ሊሆኑ የሚችል ኩባንያ በማቋቋም ሀብት መፍጠር ይገባል፡፡ የሚፈጠረው ሀብት ዩኒቨርሲቲው የያዝነውን ራእይ ለማሳካት የሚውል ነው፡፡ እነዚህ ሊፈጠሩ የሚገባቸው ኩባንያዎች የፈጠራና የምርምር ሥራዎችም ወደ ሀብት የሚቀየሩባቸው ናቸው፡፡

## 5.4. ራእይ ያለውና ተግባርን መለኪያ ያደረገ አመራር መፍጠር

የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚገነባው ራእይ ባለውና ተግባርን መሠረት ባደረገ መልኩ ራሱን እየፈተሸ ራሱን የሚያበቃ አመራር በመፍጠር ነው፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚመሰረት ነው፡፡ በመሆኑም ከትውልድ ትውልድ በሚሸጋገርና በተከታታይነት በሚያድግ ሀሳብ የሚፈፀም መሆን ይኖርበታል፡፡ ጠንካራና ራእይ ያላቸው የአመራር ስብስብ መፍጠር የሚቻልባቸው ስትራቴጂዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ. በመነሻው ላይ የተግባባ አመራር መኖር

የዩኒቨርሲቲው ታሪክ ላይ፣ አሁን ያለበትን ሁኔታና ወደፊት ሊከተለው ስለታሰበ ስትራቴጂናና ሊደረስበት ስለታቀደ ግብና ራእይ በጽሑፍ ቀርቦና ጠንካራ ውይይትና ክርክር ተካሂዶበት በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የጋራ መግባባት መፍጠር ይገባል፡፡ ይህን ተግባር ደግሞ ከአመራሩ መጀመር ይጠበቅበታል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የአመራር ስብስብ በአሁኑ ወቅት ከትምህርት ክፍል ኃላፊና ከዚያ በላይ ያሉትን በተለያዩ እርከን ያሉ በኃላፊነት ላይ ያሉትን መምህራንና ኬዝ ቲም አስተባባሪ እና ከዚህ በላይ ያሉ የድጋፍ ሰጭ ሠራተኛ ኃላፊዎች የሚያካትት ነው፡፡ እነዚህ ኃላፊዎች በዩኒቨርሲቲው ራእይ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠራቸው ወሳኝ ሲሆን መላ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን ለራዕዩ ስኬት የማሰለፍ ሚና የዚህ አመራር ተገባር ይሆናል፡፡

### ለ. የአመራር አቅም ግንባታ

ብቃት ያለውና ባለ ራዕይ አመራር የሚፈጠረው ተከታታይነት ባለው መልኩ ሚሰጥ የተግባር ስምሪት ነው፡፡ የአመራሩ አቅም የሚገነባው ተግባርን መሠረት ባደረገ መልኩ ነው ሲባል ግልጽ

ዕቅድ ከማቀ፣ ዕቅድን ከማጋራት፣ ግልጽ የሥራ ስምሪት ከመስጠት፣ የተሰጡ ሥራዎችን ከመከታተልና ከመደገፍና ውጤቱን ከመለካት አኳያ ያላቸውን ግንዛቤና አፈፃፀም በመፈተሽ ጉድለቱን በመሙላት ነው፡፡ ሁሉም በተለያዩ እርከኖች የሚሰሩ አመራሮች ግልጽ፣ ሊለካና ሊተገበር የሚችል ዕቅድ ማቀድና ይህን በሚገባ ተከታትሎ ማስፈፀም ይገባቸዋል፡፡ የአመራሩን የእይታ አድማስ ለማስፋት የተለያዩ የሀገርና የውጭ ሀገር ተቋሞች እንዲጐበኙ ማድረግ ይገባል፡፡ በተለይ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የሚጠይቀው አመራር ስብስብ በተግባር ምን እንደሚመስል እንዲያዩ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህ ሁኔታ መነሳሳትን ከመፍጠሩ በተጨማሪ ተግባራዊ ልምድ ለመቅሰም ዕድል ይሰጣል፡፡

## ሐ. ዩኒቨርሲቲውን በተከታታይ ትውልድ መገንባት የሚያስችል ስርዓት መፍጠር

የአመራር መተካካት ከትምህርት ክፍል ኃላፊ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ድረስ የማይቀርና ተፈጥሯዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በትውልድ ቅብብሎሽ ዩኒቨርሲቲውን መገንባት በሚቻልበት አግባብ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ ቁልፍ ጉዳይ በአንድ ትውልድ የተሠራውን ሥራ መሠረት በማድረግ የሚቀጥለው ትውልድ ይህን ሥራ የሚያዳብርበትና የሚያስፋፋበት ሁኔታ መፍጠርን የያዘ ነው፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለውም ደግሞ ዩኒቨርሲቲው በትውልድ ትብብሎሽ የሚዳብርና የሚስፋፋ ራእይ በመንደፍ በጊዜ በተከፋፋለ አግባብ ሊፈጸም የሚችልበት ዕድል ሲኖር ነው፡፡ በዚህ አግባብ የተከፋፈለውን ራእይ በትውልድ ቅብብሎሽ ማዳበርና መፈጸም ቀላል ይሆናል፡፡

ይህን የትውልድ ቅብብሎሽ በተሳካ ሁኔታ የምንፈጽመው ጠንካራና በመሰረታዊ የራዕይ ምሰሶዎች ላይ የተግባባ የአመራር ስብስብ በመፍጠር ነው፡፡ ይህ ስብስብ ተግባርን መሠረት ባደረገ መልኩ ስኬቱን እየገመገመና ማሻሻያዎች እያከለ በተለያዩ ትውልዶች መካከል የራእይና የሀሳብ መጋራት የሚፈጥር ይሆናል፡፡ በዚህ አግባብ በተለያዩ ጊዜያት የአመራር ቦታውን የሚወስዱ ሰዎች እንዲሁ መጠው ከባዶ የሚጀምሩ ሳይሆን በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ አውቀውና ተረክበው ይህን ሂደት የማስቀጠልና በተጠናከረና በተስፋፋ መልኩ የመፈፀም ጉዳይ ነው፡፡ በተለያዩ እርከኖች ያሉትን የአመራር ቦታዎች የሚረከቡትም ሰዎች በዋነኛነት የሚለኩት ሂደቱን በተጠናከረና በተስፋፋ መልኩ የማስቀጠል አቅማቸውንና አመለካከታቸውን መሠረት ባደረገ መልኩ ይሆናል፡፡ እነዚህን መለኪያዎች መሠረት በማድረግ ስንሠራ ከባዶ በመነሳት ሳይሆን በተለያየ ደረጃ ያለን ጉዳይ ወደሚቀጠልው የላቀ ደረጃ የሚያደርስና ለሚቀጥለው ትውልድ በበቂ ሁኔታ የሚያስረክብ ሊሆን ይገባል፡፡

# 6. ስልቶቻችን በተግባር የምንፈትሽባቸው አግባቦች

የተቀመጡት ስትራቴጂና ስልቶቻችን ተገቢ መሆን አለመሆናቸው የሚፈተሸው በሚያስገኙት ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ በተወሰነ ጊዜ የስትራተጂና ስልቶቹን አፈጻጸም መገምገምና በየጊዜው እየፈተሹ ማዳበር ይገባል፡፡ ውጤቶች ወደ አስቀመጥነው አቅጣጫ የሚወስዱ መሆኑ ከተረጋገጠና ውጤቶችም በሚፈለገው ወቅት ከተመዘገቡ ስትራቴጂና ስልቶች እየሰሩ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም እነሱን የሙጥኝ ብሎ ይዞ መቀጠል ይገባል፡፡ ነገር ግን ውጤቶች ወደ አቅጣጫችን የማይወስዱ ከሆነ ቆም ብሎ ፈትሾ ማየቱና ማስተካከሉ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ስልቶቻችንን በተግባር የምንፈትሽባቸው አግባቦችና አመላካwች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | መስፈርቶች | የተቀመጠው ግብ | በተጨባጭ ያለው አፈፃፀም |
|---|---|---|---|
| 1 | የፒ.ኤች ዲግሪ ያላቸው መምህራን በ% | 50% | |
| 2 | የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ቁጥር % | 50% | |
| 3 | በታወቁ መጽሔቶች የታተሙ ስራዎች | ሁሉም የፒ.ኤች ዲግሪ መምህራን በአመት አንድ ህትመት | |
| 4 | የምርምር ገንዘብ በ% | 40% የዩኒቨርሲቲው በጀት | |
| 5 | የምርምር መሰረ ልማት | ሁሉም የምርምር የትኩረት መስኮች በቁሳቁስ መደራጀት | |
| 6 | ለምርምር ዩኒቨርሲተ የአመራሩ ቁርጠኝነት | ከፍተኛ | |
| 7 | ለምርምር ዩኒቨርሲት ምስረታ የመምህራን መነሳሳት | ከፍተኛ | |
| 8 | ለምርምር ዩኒቨርሲቲ ምስረታ የተማሪዎች መነሳሳት | ከፍተኛ | |
| 9 | ለምርምር ዩኒቨርሲቲ ምስረታ የድጋፍ ሰጪው መነሳሳት | ከፍተኛ | |

ከላይ 1-9 የተቀመጡ መስፈርቶችን በመጠቀም የስልቶቻችንን ውጤቶች መለካትና መከታተል ይቻላል፡፡ እነዚህ አመልካች መስፈርቶች ሊዳብሩ ይችላሉ፡፡

# 7. የትውልድ ቅብብሎሽ የሚስተናገዱባቸው አግባቦች

እንደሚታወቀው ተቋምም ሆነ ሀገር የሚገነባው በትውልድ ቅብብሎሽ ነው፡፡ የትውልድ ቅብብሎሽ በሚገባ እንዴት ይፈፀማል የሚለው ጥያቄ ከባድ ነው፡፡ ከኋላም የነበረው፣ አሁንም ያለውና የወደፊቱ በጋራ ተቀምጠው አንተ ይኸን ስራ፣ እኔ ደግሞ ይህን ልስራ ብለው የሚመካከሩበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ዘመን ትውልዶች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉበትን አግባብ በጠንካራ መሰረት ላይ ለማሳረፍ ከባድ ነው፡፡ ሆኖም ግን የሰው ልጅ በተሰጠው የማሰብ ልዩ ፀጋ ተጠቅሞ በትውልድ ሽግግር ሊፈፀሙ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የመንደፍ አቅም አለው፡፡ በዚህ መሠረት እኛም አሁን ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን በታሪክ አጋጣሚ የምናቀሳቅስ የዚህ ዘመን ትውልዶች ይህ ተቋም በትውልድ ቅብብሎሽ እንዴት ሊገነባና ሊያድግ ይችላል፣ አንዱ የሰራውን ሌላኛው ትውልድ ሳያፈርስና ይልቁንም የወደፊት መሠረቱ በሚሆን አግባብ ተጠቅሞበት ተቋሙን ቀጣይነት ባለው ዕድገት ውስጥ ማስገባት ይችላል ብሎ በመጠየቅ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ይህ የተቀመጠ አቅጣጫ ትውልድ ተሻጋሪ በሆነ አግባብም ሆነ በተወሰነ ጊዜ ሊያገለግል ይችላል፡፡ ነገር ግን የአሁኑ ትውልድ በምን አግባብ እያሰበ እንደሚሰራና የመጪው ትውልድ የኛን ስራ ውጤት በተጨማሪነት እንዲያገለግለው ሊከተለው የሚገባን አግባብ ማሳየቱ ተገቢ ነው፡፡

አንድ ትውልድ ከሱ በፊት በነበሩ ትውልዶች ዕውቀት፣ ክህሎትና አጠቃላይ ባህል መሠረት የሚገባ ነው፡፡ ከሱ በፊት ከነበሩ ትውልዶች በወረሰው ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህል ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ መቀጠል ግን ያዳግተዋል፡፡ ወቅቱ ያመጣቸው አዳዲስ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ስለሚኖሩ እንደ ወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ የራሱን ዕውቀት፣ ባህልና ክህሎት ይጨምራል፡፡ ጊዜ ያለፈባቸውንና ከወቅቱ ጋር የማይሄዱትን ከበፊት ትውልዶች የወረሳቸውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህልም ሊተው ይችላል፡፡ ይህ ማለት በትውልድ ሽግግር ወቅት የሚደመሩ፣ የሚቀነሱና እንዳለ የሚቀጥሉ ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህል አሉ ማለት ነው፡፡ ትውልድ ተሻጋሪ ሀሳቦች የሚባሉት ሁኔታዎች ቢቀያየሩም የሚሰሩ ሀሳቦች ማለታችን ነው፡፡ በዚህ መንገድ ስናስብ የኛ ትውልድ በሁሉም በተከታታይ ትውልዶች ትኩረት አግኝቶ የሚቀጥለው ትውልድ ተሻጋሪ አስተሳሰብ የሚመስለን የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን በየጊዜው ለሚመጣው ትውልድ የጥንካሬ ምንጭ ሆኖ ጉልህ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ አንቀሳቃሽ ሞተር እንዲሆን የማብቃቱን እሳቤ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዚያት የሚኖሩ ትውልዶች ከነሱ በፊት የነበረውን ትውልድ እሳቤዎች የሚማሩበት፣ በነሱ ወቅት ያሉትን ተጨባጭ

ሁኔታዎች የሚፈትሹበትና ተገቢ አሠራር የሚፈጥሩበት እንዲሁም ከነሱ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ሽግግሩን በሚገባ የሚፈጽሙበትን አግባብ የሚወያዩበት ተቋም ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ በተለያዩ ጊዜያት የመጡና ወደፊትም የሚመጡ ትውልዶች ዕውቀት፣ ቴክኖሎጂና ባህል እርስ በርሳቸው የሚገናኙበትና በየጊዜው ለሚፈጠረው ሁኔታ ተገቢ የሆነው ዕውቀት፣ ቴክኖሎጂና አጠቃላይ አመለካከት የሚለይበት ተቋም ይሆናል። በኛ ግምት ራዕይ ጥበብ 2017 ብለን የጀመርነውና እየተገበርን ያለው ራዕይ በተከታታይ ለሚመጡ ትውልዶች አንድ መሠረት ይሆናቸዋል ብለን እናስባለን። በዚሁ አጋጣሚ አንድ ታምር ተፈጥሮ ጽሁፉችን ካልጠፉ በስተቀር ከብዙ መቶ አመት በኋላም ቢሆን የሚመጡ ትውልዶች የኛን እሳቤ በአጭሩ በዚህ ሰማያዊ መጽሐፉችን ያገኛሉ። ሲያነቡትም እኛ እንዲሁ በአንድ ዘመን ብቅ ብለን የራሳችንን ጥቅም ስናሳድድ ኖረን የጠፋንና ዱካችን የማይገኝ ግብዞች ሳንሆን በገባን መጠን ለከታታይ ትውልዶች በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ብልጽግና እንዲኖረው በማሰብ በገባን ልክ መስራታችንን ይገነዘባሉ።

በመጨረሻም የትውልድ ቅብብሎሽ በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ በተለያዩ ጊዜያት የሚኖሩ ኃላፊዎች፣ መምህራንና ሠራተኞች የሚጽፏቸው ጽሑፎች የተለያዩ ትውልዶች አሻራ ስለሆኑ በጣም ጠቃሚ ናቸው። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲንም የሚመሩና ውስጡ የሚሰሩ ዜጎች ይህን ስራ ቀጣይነት ባለው መልኩ በመስራት የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ግንባታ በትውልድ ቅብብሎሽ እንደሚፈፀም ተስፋችን ትልቅ ነው።

# 8. የክትትልና ድጋፍ ስርዓት

ይህ ራእይ ሊፈጸም የሚችለው  አመራሩ ማስፈጸሚያ ስልቶቹንና ግቦቹን ጠንቅቆ በመረዳት፣ ከራዕዩ አንፃር በዝርዝር በመተንተን ተደጋጋፊ ዕቅዶችን በመንደፍ፣ አፈፃጸማቸውን በተጠናከረ አግባብ ሲከታተልና ሲደግፍ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዋነኛው ፈፃሚ ኃይል የሠው ኃይሉ በመሆኑ በአካዳሚኩም ሆነ በአስተዳደር ዘርፍ ያለው የሠው ኃይል ተገቢው ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት፣ ከሥራ ተነሳሽነትና ተቋማዊ ተቆርቋሪነት ጋር እንዲፈጠር ማድረግ ከተቻለ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱ ይህን መሰረታዊ ጉዳይ የጨበጠና ሁሉም ተግባራት  ተሳስረው እየተፈጸሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱ አራት ግቦች ይኖሩታል፡፡

- በዩኒቨርስቲው የታቀዱ ተግባራት በጥራት፣ በእቅዱ አቅጣጫ መሰረትና የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- መምህራን፣ ተመራማሪዎችና የአስተዳደር ሰራተኛው የተሰማሩበትን ተልዕኮ በመፈጸም ለተልኮአቸው በአመለካከትና በክህሎት እየተገነቡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በአፈጻጸም ሂደት የተገኙ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለቀጣይ ተልዕኮ በግብአትነት መጠቀምና እየተማረ የሚሄድ የዩኒቨርስቲ አቅም እየተገነባ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የዩኒቨርስቲው ያስቀመጣቸው ተግባራት በተመራማሪውና በተማሪው እንዲሁም በአስተዳደር ሰራተኛው ሲፈጸም ተቋማዊ አቅም በሚገነባ አግባብ መሆኑን መከታተል፣

# ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን የራዕይ ጥበብ 2017 መንገድ በወፍ በረር እይታ አቅርበናል፡፡ አንድ ህንፃ ሲገነባ ሲታሰብ የራሱ የሆነ ንድፍ እንዳለው ሁሉ ይህ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የተነደፈበት ሰነድ ነው፡፡ የህንፃው ንድፍ በአንዴ ተሰርቶ እንደማይጠናቀቅና በግንባታው ሂደትም ነባራዊ ሁኔታዎቹ እየታዩ የሚሰተካከልበት ዕድል እንዳለው ሁሉ ዩኒቨርሲቲያችን በቀጣይ አገራዊና አለማቀፋዊ ፋይዳ ያላቸው ውጤቶች እንዲመነጩበት ለማድረግ የሚከተለው ይህ መጽሐፍም በነባራዊ ሁኔታዎች ተመስርቶ ማስተካከል ሲያስፈልግ እየተስተካከለና እየዳበረ ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዩኒቨርሲቲውን በተመለከተ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ሁሉ ይህን ሰነድ የማዳበር ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ደግሞ ይዘቱን በመረዳት ለስኬቱ እንዲረባረብ ይጠበቃል፡፡

በመሆኑም የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የራዕይ ጥበብ 2017 መንገድ ይህ ነው፡፡

**መልካም ጉዞ!**